# የኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር አካል በኖርዌይ ያደረጉት የሥራ ጉብኝትና ህዝባዊ ስብሰባ በስኬት ተጠናቀቀ

በመጀመሪያ ከኖርዌይ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የምሥራቅና የምዕራብ አፍሪካ አገራት ኃላፊዎች፣ ከላንድኢንፎ፣ ከኖርዌይ ኢሚግሬሽን ዳይሬክቶሬት የኢትዮጵያ ክፍል ኃላፊ፣ የስደተኞችን ጉዳይ ከሚያየው ክፍልና ከኖርዌይ የስደተኞችን መብት ከሚያስከብረው ከተቋም ጋር ሰፊ ውይይቶችን በተለያዩ ቀናት አካሂደዋል። በነዚሁም ውይይቶች ባለው ተጨባጭ ሁኔታና ኢሕአፓ እያደረገ ባለው ትግል ዙሪያና በውያኔ የግፍ አገዛዝ ምክንያት ለስደት እይተዳረጉ በኖርዌይ ስላሉት ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችንና የድርጅታችን አባላት የስደተኞች መብት መከበር ጉዳይ በሰፋትና በጥልቀት ተወያይተዋል።

የካቲት 11 ቀን 2009 ዓም ኢሕአፓ ኖርዌይ ክፍል የህዝብን የተለያዩ ብዥታዎች እና ወቅታዊ የሃገራችንን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ህዝባዊ ውይይት ማድረጉ ብዙ ያስተምራል ብሎ በማመን ለዚህም ይመጥናሉ ያላቸውን እንግዶች በመጋበዝ እድምተኞችን የማረከ ለነበራቸው ጥያቄዎች መልስ የሚሆን ግንዛቤን የሚያስጨብጥ ሆኖ እንደታሰበውም አስተማሪ ሆኖ አልፏል። ከተጋበዙት እንግዶች መካከል ከኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር አቶ  እያሱ አለማየሁ በሃገራችን ወቅታዊ ሂደት ላይ፤ አሁን ባለው የህዝብ ትግል ላይ፤  የወያኔን የመከፋፈል ሴራ፤  የህብረትን በጎነት አሁን ላይ ያለን እንቅፋት ሌሎችንም አንስተው ህዝብን በሚማርክ በሚቀሰቅስና  በሚያስተምር ሁኔታ ሃሳባቸውን አብራርተዋል።

ጸሃፊው እና የምስራቅ አፍሪካ  ኤክስፐርት የሆኑ አቶ ዩሱፍ ያሲን እና  ወጣቱ ዶ/ር ተክሉ አባተ የማንነት ፖለቲካ፤ ብሄርተኝነት፤ የኢትዮጵያ እጣ ፈንታ እና የአማራው ፖለቲካዊ ንቅናቄ እና አንድምታው በሚል ርእስ ላይ ከወትሮው ለየት ባለና ጠለቅ ያለ  ይዘት ያለው ትንታኔ  አቅርበዋል።

የነሡን ሃሳብ ተመርኩዘውም ታዳሚዎች በርካታ  ጥያቄዎችን ያነሱ ሲሆን ለጥያቄያቸውም አጥጋቢ ምላሽን አግኝተዋል። በዚህ ስብሰባ  በቁጥር በርካታ የሆኑ በኦስሎ እና  በተለየዩ የኖርዌይ ክፍለሃገራት የሚገኙ ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ተሳታፊ ሆነዋል። ብዙዎችም በስብሰባው መርካታቸውንና መደገም እንዳለበት በአስተያየታቸው ገልጸዋል።

በዚህ ህዝባዊ ስብሰባ ላይ ሌሎችም የተለያዩ ዝግጅቶች ቀርበዋል። ከነዚህም ውስጥ ከኖርዌይ ኢወክንድ እና ሴቶች ክፍል ወጣት አሚናት ኢብራሂም የታዳማዎችን ቀልብ በሳበ መልኩ ባደረገችው ንግግሯ ለወጣቱ እና ለሴቶች የትግል ጥሪዋን አቅርባለች።

ከዚህም በተጨማሪ ገቢው ለፍኖተ ሬድዮ የሚውል የጨረታ ፕሮግራም የተካሄደ ሲሆን ከዚህም ሌላ የምሳ ፕሮግራም በገንዘብ ተደርጎ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ተደርጓል። ውጤቱም እጅግ የሚያስደስት አብዛኛው እድምተኛ እንደተሳተፈበት ለማወቅ ተችሏል።

እንደዚህ ያለ ረዘም ያለ ፕሮግራም ሲኖር በግጥሙ በለስላሳ ሙዚቃው እና ማራኪ ክራር አጨዋወቱ ታዳሚውን ዘና የሚያደርገው እንዳለ ህዝቡን ዘና እያደረገ አቆይቶታል።
የኢሕአፓ ኖርዌ ክፍልም ባደረገው ዝግጅት ከበርካታ ታዳሚዊች የምስጋና መልእክቶች ደርሰውታል። የኢሕአፓ ኖርዌይ ክፍል አመራርም ጥሪውን አክብረው ለመጡት በሙሉ ምስጋናውን አቅርቧል።




MARTYRS
OF
ETHIOPIA
MURDERED
BY
MARTYRS
OF
BY


MARTYRS
OF
ETHIOPIA
MURDERED
BY
TPLF
GEMORAW HAILU
MARTYRS
OF
ETHIOPIA
MURDERED
BY
TPLF

0